

FOUNDATION FOR BLACK COMMUNITIES

# የአመልካች መመሪያ

## ብላክ አይዲያስ ግራንትስ፡ ብሪጅ ኤንድ ቢልድ

2023

Funded in part by the Government of Canada's Black-Led Philanthropic Endowment Fund

Canada

# ስለ ፋውንዴሽን ፎር ብላክ ኮሚዩኒቲ መረጃ

ጥቁር ማህበረሰቦች የበጎ አድራጎት አሰራርን በተመለከተ አዲስ አቀራረብ እንዲኖር ለረጅም ጊዜ ጥሪ ሲያደርጉ ቆይተዋል። ለዚህ ጥሪ ምላሽ ለመስጠትና ሁሉም ጥቁር ግለሰቦችና ማህበረሰቦች እንዲጎለብቱና የራሳቸውን የወደፊት እጣ ፈንታ ለማበጀት የሚያስችላቸው ተወካይ / አካል እንዲኖራቸው በማሰብ በ*2020* የፋውንዴሽን ፎር ብላክ ኮሚዩኒቲስ *(ኤፍ.ኤፍ.ቢ.ሲ./FFBC)* ተቋቋመ። የዚህ ፋውንዴሽን ዋና ተልዕኮ የጥቁሩን ማህበረሰብ ህይወት መሰረታዊ በሆነ መንገድ መለወጥና ማሻሻል ነው። ኤፍ.ኤፍ.ቢ.ሲ. ጥቁሮች ላይ ትኩረት የሚያደርግ የካናዳ የበጎ ተግባር ፋውንዴሽን ሲሆን ሙሉ ጥረቱም በጥቁሮች የሚመሩ፣ ጥቁሮች ላይ ያተኮሩና፣ ለጥቁሮች አገልግሎት የሚሰጡ ድርጅቶች በህብረተሰቡ ላይ ትርጉም ያለው ለውጥ እንዲያመጡ የሚያስቸላቸውን ዘላቂ ድጋፍ ማግኘታቸውን ማረጋገጥ ነው።

# ብላክ አይዲያስ ግራንትስ፡ ብሪጅ ኤንድ ቢልድ 2023

የኤፍ.ኤፍ.ቢ.ሲ. ብላክ አይዲያስ ግራንትስ፡ ብሪጅ ኤንድ ቢልድ 2023 ፕሮግራም ከፍተኛ የሆነ የ8.9 ሚሊየን ዶላር በጀት ያለው ሲሆን፣ በካናዳ ጥቁር ማህበረሰቦች ለሚመሩ መፍትሄ–ተኮር ፕሮጀክቶች እውቅናና ድጋፍ ይሰጣል። ይህ የሙከራ ፕሮግራም ለጥቁሩ ማህበረሰብ አስቸኳይና ቀጥተኛ የሆኑ አንዳንድ ፍላጎቶችን ለማገዝ ከመደገፍ ባሻገር ወደፊት ለሚኖሩ የድጋፍ ፕሮግራሞችም ጠቃሚ ትምህርት ለመቅሰም ይረዳል።

የብሪጅ ኤንድ ቢልድ ፈንድ ለአንድ አመት የሚዘልቅ ድጋፍ በመስጠት በጥቁር–የሚመሩ፣ ጥቁር–ተኮርና ጥቁር–አገልጋይ የሆኑ የበጎ አድራጎትና ለትርፍ ያልተቋቋሙ ድርጅቶች ጸረ–ጥቁር ዘረኝነትን ሲታገሉና የህብረተሰቡን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች ለማሻሻል ጥረት ሲያደርጉ አቅማቸውን እንዲያጎለብቱ ድጋፍ ያደርጋል።

**ፈንዱ ማመልከቻ መቀበል የሚጀመረው በዲሴምበር 18, 2023 ሲሆን፣ የመጨረሻው ማመልከቻ መቀበያ ቀን ፌብሪዋሪ 1, 2024 ከምሽቱ 11:59 በፓሲፊክ ሰአት አቆጣጠር ነው።**

Funded in part by the Government of Canada's Black-Led Philanthropic Endowment Fund
Canada

# አቀራረባችን

ኤፍ.ኤፍ.ቢ.ሲ. በአይነቱ የመጀመሪያ ድርጅት ሲሆን ግቡም የጥቁሩን ማህበረሰብ የመፍትሄ ሰጪነት አቅም መረዳትና እውቅናና ክብር መስጠት ነው። በቅድሚያ ግን ወደፊት የሚኖሩ ፕሮግራሞችና ድጋፎች (ፈንድስ) በጥሩ ግንዛቤ ላይ የተመሰረቱ እንዲሆኑ ለማድርግ ከህብረተሰቡ መማር ግድ ይለናል። ይህንንም ለማሳካት የጥቁርን ማህበረሰብ ድምጽና የሙያ ብቃት እንሻለን። ኤፍ.ኤፍ.ቢ.ሲ. አሳታፊ ድጋፍ አሰጣጥ ሞዴልን ተቀብሎ የሚተገብረውም የህብረተሰቡ ተሳትፎ ያለውን ከፍተኛ ጥቅም በመገንዘቡ ነው። አሳታፊ የድጋፍ አሰጣጥ ፍልስፍና መሰረቱ ሁላችንም የተሳሰርን ስለሆን በአካባቢያችን ያሉትን ሌሎች ሰዎች ሁኔታ ስናሻሽል ለራሳችንም ጭምር ሁኔታዎችን እናሻሽላለን የሚል ነው።

ይህ አቀራረብና አሰራር ፕሮግራሙ ሊያስገኘው ለሚፈልገው ውጤት በሃሳብ ቅርብ ለሆኑ ሁሉ ለሚኖራቸው አስተያየት፣ እውቀት፣ ልምድና፣ የፈጠራ ችሎታ ከፍተኛ ትኩረት ይሰጣል። ሁሉም ማመልከቻዎች አመልካቾችም ጭምር በሚሳተፉበት ከጥቁሩ ማህበረሰብ በተውጣጡ ሰዎች ስብስብ ይገመገማሉ። አሳታፊ ድጋፍ አሰጣጥ ተአማኒነትን፣ ፍትህንና ድጋፍን/ተጠሪነትን (ኤጀንሲ) የፍልስፍናው ማዕከል አድርጎ ይመለከታል። ኤፍ.ኤፍ.ቢ.ሲ. የበጎ አድራጎት ሥራን ከተለመደው አሰራር ለመለወጥና ዲሞክራሲያዊ ለማድረግ ይህን ሞዴል ይጠቀማል ።

ኤፍ.ኤፍ.ቢ.ሲ. ታሪካዊና ጠቃሚ የሆነ የአካባቢ ፍትህ፣ የአካል ጉዳተኝነት ፍትህ፣ የሥነ-ጾታ/ጄንደር ፍትህ፣ 2ኤስልጂቢቲኪው+ና የመሳሰሉ ብዙ መሰናክሎችና ድጋፍ ለማግኘት ከፍተኛ ችግር ያለባቸው የማህበረሰብ ክፍሎችን ለመደገፍ የተከናወኑ በርካታ ታሪካዊና ጠቃሚ ሥራዎች መኖራቸውን ያውቃል። እነኚህም ማህበረሰቦች ሴቶችና ልጃገረዶች፣ ጾታ የለወጡ፣ የአካል ጉዳተኞች፣ አነስተኛ ገቢ ያላቸው፣ መናገር የማይችሉ፣ ከሌላ ሀገራት ካናዳ የመጡ (ማይግራንት)፣ እስረኛ የነበሩና በቂ ምግብ ለማግኘት የሚቸግራቸው ሰዎችን ያካትታል። ኤፍ.ኤፍ.ቢ.ሲ. ድልድይ በመሆን የተለያየ ትኩረት ቢኖራቸውም  ጨቋኝነትን ከሚቃወሙ፣ ከቅኝ-ግዥ ነጻ መሆንንና ፍትሀዊ አሰራርን ከሚደግፉ ስብስቦች ጋር በመተባበር ጥቁር ማህበረሰቦች በሙሉ በአቅም እንዲጎለብቱ ለማድረግ ይሰራል። ይህ ብሪጅ ኤንድ ቢልድ ፈንድ የተቀረጸው ከህብረተሰቡ በተገኘ ሀሳብ ላይ ሲሆን የአሁኑ የሙከራ ፕሮጄክት ወደፊት ለሚኖሩ የረጅም ጊዜ ድጋፍ ያላቸውፕሮጀክቶች  ብዙ የሚማሩበት እንደሚሆን ኤፍ.ኤፍ.ቢ.ሲ. ያምናል።



Funded in part by the
Government of Canada's Black-Led
Philanthropic Endowment Fund
Canada

# ለማመልከት ብቁ መሆን (መመዘኛዎችን ማሟላት)

## መመዘኛውን የሚያሟሉ ድርጅቶች

ለብሪጅ ኤንድ ቢልድ ድጋፍ ማመልከት የሚችሉት መመዘኛዎቹን ያሟሉ ድርጅቶች ብቻ ናቸው። መመዘኛውን አሟልተው ለመገኘት ድርጅቶች የሚከተለው ይጠበቅባቸዋል፤

- ✓ **ጥቁር-መር፣ ጥቁር-ተኮር፣ ጥቁር-አገልጋይ መሆን (ቢ3)። ይህ ማለት በሁሉም የአመራር እርከን ላይ ያሉት አብዛኛዎቹ ጥቁሮች ናቸው። የድርጅቱ ዋና ግብም ለጥቁሮች ትርጉም ያለው ድጋፍ መስጠትና ጥቁሮችን ማሳተፍ ሲሆን አብዛኛዎቹ የድርጅቱ ፕሮግራሞችና እንቅስቃሴዎች ቅድሚያ ትኩረታቸው ለጥቁሮች አገልግሎት መስጠት ላይ ነው።**

  ይህ ፋውንዴሽን ፎር ብላክ ኮሚዩኒቲስ ለጥቁር-መር፣ ጥቁር-ተኮር፣ ጥቁር-አገልጋይ መሆን ያለው አመለካከት የሚወሰደው ከህብረተሰቡ በመማርና ከጊዜ ወደጊዜ አሰራሩን ለማሻሻል ከልምድ መማር ላይ በማተኮር ነው። ለድጋፍ ጥያቄ የሚያስገቡ በሙሉ ድርጅታቸውና ያቀዱትፕሮጄክት እንዴት ጥቁር-መር፣ ጥቁር-ተኮርና፣ ጥቁር-አገልጋይ እንደሆኑ በዝርዝር ማስረዳት ይጠበቅብቸዋል።

- ✓ **በበጎ አድራጎት ድርጅትነት የተመዘገበ ድርጅት፣ ኢንኮርፖሬትድ የሆነ (ማለትም ህጋዊ ሰውነት ያለው) ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት፣ ሌላ ድጋፍ ተቀባይ ለመሆን ብቁ ሆኖ የተገኘ ድርጅት ወይንም የራሱ ህጋዊ ሰውነት ሳይኖረው ህጋዊ ሰውነት ካለው ለትርፍ ካልተቋቋመ ድርጅት ጋር በመተባበር የሚሰራ። ኢንኮርፖሬትድ ያልሆኑ (ህጋዊ ሰውነት የሌላቸው) ስብስቦች የጥቁር ትብብሮች፣ የተማሪዎች ማህበራት፣ ተዛማጅ ቡድኖችንና የመሳሰሉትን ያካትታል።**

- ✓ **አድራሻው (የሚገኝበት) ካናዳ ውስጥ የሆነ።**

Funded in part by the Government of Canada's Black-Led Philanthropic Endowment Fund
Canada

## መመዘኛውን የሚያሟሉ ፕሮጀክቶች / ሥራዎች

ማመልከቻውን በሚያዘጋጁበት ወቅት ምን አይነት እንቅስቃሴዎችን ማከናወን እንደሚፈልጉ የማብራራት እድል ይኖርዎታል። ድጋፍ የሚያገኙት አመልካቾችና ፕሮጀክቶች መመዘኛውን የሚያሟሉ ብቻ ሲሆኑ መሟላት ያለባቸው መመዘኛዎችም የሚከተሉት ናቸው።

- ✓ **ቢያንስ ከሶስቱ አንዱን የብሪጅ ኤንድ ቢልድ ፈንድ የትኩረት አቅጣጫዎች ላይ ያተኮረ: ማለትም ጸረ-ጥቁር ዘረኝነትን መዋጋት፣ ማህበራዊ ውጤቶችን ማሻሻልና፣ እኮኖሚያዊ ውጤቶችን ማሻሻል ከሚሉት ውስጥ ቢያንስ በአንዱ ላይ ያተኮረ፣**

- ✓ **አንድ ወይንም ከዚያ በላይ** [የዘላቂ እድገት ግቦችና (ሰስቴይኔብል ዴቭሎፕመንት ጎልስ)]() **እና** [የጤና ደረጃን የሚወስኑ ማህበርዊ ጉዳዮች (ሶሻል ዲተርምናንትስ ኦፍ ኸልዝ)]() **ላይ ያተኮረ፣**

- ✓ የታቀደው ፕሮጄክት ባለው የጊዜና የበጀት ገደብ ውስጥ መጠናቀቅ መቻል። **ሙሉ በጀቱ ሥራ ላይ መዋል ያለበት ማርች 31፣ 2025 ከማለፉ በፊት** ነው።

- ✓ **ዝቅ ብሎ የተዘረዘሩትን መመዘኛዎች የማያሟሉ ፕሮጀክቶች /ሥራዎችን ያላካተተ።**

**0ኢንኮርፖሬትድ ያልሆኑ ለትርፍ ያልተቋቋሙ ድርጅቶች፣ ትብብሮችና ቡድኖች**

ኢንኮርፖሬትድ ያልሆኑ ለትርፍ ያልተቋቋሙ ድርጅቶች፣ ትብብሮችና ቡድኖች ከኤፍ.ኤፍ.ቢ.ሲ. ፈንድ ድጋፍ ለማግኘት ኢንኮርፖሬትድ ከሆኑ ለትርፍ ያልተቋቋሙ ድርጅቶች ጋር በጥምረት መስራትአለባቸው። ማመልከቻውን በሚያስገቡበት ወቅት ኢንኮርፖሬትድ የሆነ ተባባሪ ድርጅት ባይኖርዎትም ማመልከቻውን እንዲያስገቡ ይበረታታሉ። ኤፍ.ኤፍ.ቢ.ሲ. ኢንኮርፖሬትድ ያልሆኑ ለትርፍ ያልተመሰረቱ ደርጅቶች ኢንኮርፖሬትድ ከሆነው አጋር ድርጅት ጋር የትብብር ስምምነት እንዲፈራረሙ ይጠይቃል። ይሄም ስምምነት የትብብሩን አላማ በግልጽ ማስቀመጥ ይኖርበታል።

ድጋፉን ለማግኘት ኢንኮርፖሬትድ ያልሆኑ ለትርፍ ያልተቋቁቅሙ ድርጅቶች ትብብሮችና ቡድኖች በሙሉ ከፌብሪዋሪ 1 2024 በፊት ኢንኮርፖሬትድ የሆነ ተባባሪ ሊኖራቸው ይገባል። የሚያስፈልገውን መመዘኛ ማሟላትን በተመለከተ ተጨማሪ ጥያቄ ካለዎት እባክዎን በዚህ አድራሻ ያግኙን fund@forblackcommunities.org.

Funded in part by the Government of Canada's Black-Led Philanthropic Endowment Fund
Canada

## መመዘኛውን የማያሟሉ ድርጅቶች

ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ድርጅቶች የኤፍ.ኤፍ.ቢ.ሲ.ን ፈንድ ድጋፍ ለማግኘት የሚያስፈልገውን መመዘኛው አያሟሉም፡

- በጥቁር የማይመሩ፣ ጥቁር ተኮር ያልሆኑ፣ ጥቁር አገልጋይ ያልሆኑ ድርጅቶች፣
- ለትርፍ የተቋቋሙ ድርጅቶችና ኮርፖሬሽኖች፣
- ግለሰቦች፣
- የንግድ ተቋማት፣ የንግድ ማህበራት፣ የንግድ ምክር ቤትና (ቻምበር ኦፍ ኮሜርስ) የኮንዶሚኒየም ማህበራት፣
- ሆስፒታሎች፣ የጤና ተቋማትና፣ ትምህርት ቤቶችን ጨምሮ የክፍለ ሀገራትና ቴሪተሪዎች አካላት፣ የግል ትምህርት ቤቶች፣ ዩኒቨርስቲዎች፣ ኮሌጆች፣ የጤና ባስልጣናት፣ የጤና አጠባበቅ ባልስጣናት፣ የትምህርት ተቋማት እንዲሁም የጤናና ማህበራዊ አገልግሎት ተቋማት፣
- መዘጋጃዎችና በስራቸው የሚገኙ አካላት፣ የአካባቢ አስተዳደር፣ የአካባቢ ክልሎችን ጨምሮ በመዘጋጃዎች አስተዳደር ስር ያሉ ተቋማት፣ እና
- ቀዳሚ እንቅስቃሴው በማንኛውም የፖለቲካ ስራ ላይ ያተኮረ ፓርቲ የህዝብ ተወካይና እጩ የህዝብ ተወካይን በመደገፍ ወይንም በመቃውም ተግባር የተሰማራ፣



## መመዘኛውን የማያሟሉ ፕሮጀክቶች / ስራዎች

ከዚህ በታች የተዘረዘሩት እንቅስቃሴዎች የኤፍ.ኤፍ.ቢ.ሲ.ን ፈንድ ድጋፍ ለማግኘት መመዘኛውን አያሟሉም:

- የበጀት ጉድለትን መሸፈን፣
- አልኮል መጠጥ ወይንም ሀሺሽ ለመግዛትና ለመሸጥ፣ ከእነኚህ ተግባራት ጋር የተያያዘ ፈቃድ ወይንም ላይሰንስ ለማውጣት፣ ለአልኮል መጠጥና ሀሺሽ መሸጫ ስፍራ ወይንም እነኝህን እንቅስቃሴዎች ለማመቻቸት ተቋማትን/ሀንጻዎችን ማደስና መጠገን፣
- ማንኛውንም የፖለቲካ ፓርቲ፣ የህዝብ ተወካይና፣ እጩ የህዝብ ተወካይን የሚደገፍ ወይንም የሚመቃውም ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ፣
- ሀይማኖታዊ የሆኑ እንቅስቃሴዎች ወይንም በማንኛውም ሀይማኖታዊ ዘርፍ መሳተፍን ግዴታ የሚያደርጉ ሁኔታኦች (ለምሳሌ: ማህበረሰብን መሰረት ላደረገ የምግብ አገልግሎት (ኮሙኒቲ ኪችን) ቁሳቁስና ሰራተኛ ወጪ መሸፈኛ ድጋፍ ሀይማኖታዊ ተቋማት ማግኘት የሚችሉ ሲሆን ዋና ተግባሩ ሀያማኖታዊ የሆነ እንቅስቃሴ ግን ድጋፍ አያገኝም)፣
- ዋና አገልግሎቱ ለሃይማኖታዊ አምልኮ ለሆነ ተቋም ጥገናና እደሳ፣
- የገንዘብ ማሰባሰብና ካፒታል የማግኛ ዘመቻ እንቅስቃሴዎች በሙሉ፣
- ካናዳ ለሚኖሩ ጥቁሮች የሚጠቅም ፕሮግራም እንቅስቃሴና አገልግሎት የማይሰጡ፣
- ከካናዳ ውጪ የሚከናወኑ እንቅስቃሴዎች ፕሮግራሞችና አገልግሎቶች፣ እንዲሁም
- የኤፍ.ኤፍ.ቢ.ሲ. ድጋፍ ኮንትራት ላይ ከተጠቀሰው የፕሮጀክት መጀመሪያ ቀን በፊት የተጠናቀቁ ተግባራትና ወጪዎች፣



Funded in part by the
Government of Canada's Black-Led
Philanthropic Endowment Fund

# ለጥቁር ማህበረሰቦች የሚያስፈልጋቸውን ድጋፍ ማድረግ

## የገንዘብ የድጋፍ ዘርፎች

የብሪጅ ኤንድ ቢልድ ፈንድ መመዘኛውን ከሚያሟሉ ቢ3 ድርጅቶች በተለያየ የአፈጻጸም ደረጃ ላይ ያሉ በጥቁሩ ማህበረሰብ ላይ በጎ ተጽእኖ የሚኖራቸው ፕሮጀክቶችንና ፕሮግራሞችን በተመለከተ የድጋፍ መጠየቂያ ማመልከቻዎች ይቀበላል፡፡ ለዚህም ሶስት የድጋፍ ዘርፎች አሉት፡፡ እባክዎን ከድርጅትዎ ወይንም ቡድንዎ የአሁን ፍላጎት ጋር የሚጣጣመውን የድጋፍ ዘርፍ ይምረጡ፡፡ ሶስቱ የድጋፍ ዘርፎች የሚከተሉት ናቸው፤

**መሰረታዊ የድጋፍ ዘርፍ እስከ $40,000 ከፕሮግራም ጋር ያልተያያዙ መሰረታዊ ስራ ማከናወኛ ፍላጎቶች፤**

**የማሳደጊያ ድጋፍ ዘርፍ ከ$40,000 እስከ $100,000 አዳዲስ ሀሳቦች ወይንም ከአሁን ቀደም ያሉ ሀሳቦችን ፕሮግራሞችንና አገልግሎቶችን ማስፋፊያ፤**

**የማህበረሰብ መዋዕለንዋይ (ካፒታል ) ድጋፍ ዘርፍ እስከ $250,000 የሚደርስ ማህበራዊ መሰረታዊ ልማትና መዋዕለንዋይ ሥራዎች ማከናወኛ**

Funded in part by the
Government of Canada's Black-Led
Philanthropic Endowment Fund
Canada

## የመሰረታዊ ድጋፍ ዘርፍ | እስከ $40,000

ከፕሮግራም ጋር ያልተያያዙ መሰረታዊ ስራ ማስኬጃ ፍላጎቶች


መመዘኛውን የሚያሟሉ ድርጅቶችና ቡድኖች ያላቸውን የመሰረታዊ ወጭ ፍላጎት ለመሸፈን እስከ $40000 የሚደርስ ድጋፍ መጠየቅ ይችላሉ። ይህ ድጋፍ ድርጅቶችና ቡድኖች ከመሰረታዊ እንቅስቃሴዎቻቸው ጋር የተያያዙና ውጤታማነታቸውን ለማገዝ የሚችሉ እንቅስቃሴዎችን ለመደገፍ የሚጠቅሙት ይሆናል። አመልካቾች ከፕሮግራሞቻቸው ጋር ላልተያያዙ አስተዳደራዊ ለሠራተኛና ለሠራተኛ-ያልሆነን ወጪ መሸፈኛ ማመልከቻ (ፕሮፖዛል) ማስገባት ይችላሉ።

**ምሳሌዎች**

- አንድ ቢ3 ድርጅት በተለይ ጥቁር ማህበረሰቦችን ለሚያግዝ ፕሮግራም ሰራተኛ ለመቅጠር ድጋፍ ይጠይቃል፣
- አንድ የጥቁር ወጣቶች ቡድን አስተዳደራዊ መዋቅራቸውን የሚያዘጋጅላቸው አማካሪ ለመቅጠር ድጋፍ ይጠይቃል፣
- አንድ የበጎ አድራጎት ድርጅት አዳዲስ የቢሮ እቃዎች ለመግዛት ድጋፍ ይጠይቃል፣
- አንድ ቢ3 ድርጅት የመረጃ ቴክኖሎጂና መሳሪያዎችን ይገዛል፣

Funded in part by the
Government of Canada's Black-Led
Philanthropic Endowment Fund
Canada

## የማሳደጊያ ድጋፍ ዘርፍ | ከ$40,000 እስከ $100,000



አዳዲስ ሀሳቦችን ወይንም ነባር ፕሮግራሞችንና አገልግሎቶችን ማስፋፊያ

መመዘኛውን የሚያሟሉ ድርጅቶችና ቡድኖች አዳዲስ ሀሳቦችን ወይንም ከአሁን ቀደም ያሉ አሰራሮችን በመፈተሽ የጥቁር ማህበረሰቦችን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ደህነንት ለማሻሻል ምርምር፣ ዲዛይን፣ ሙከራና የግምገማ እቅስቃሴዎች ለማከናወን ከ*$40,000* እስከ *$100,000* ለሚደርስ ድጋፍ ማመልከት ይችላሉ።

- **አዳዲስ ሀሳቦችና አሰራሮች፡** አዲስ ፕሮግራሞችንና አገልግሎቶችን የሚያዘጋጁና የሚጀምሩ፣ አዳዲስ አስተሳሰቦችንና አሰራሮችን የሚፈትሹ የሚሞክሩ ወይንም በሥራ ላይ የሚያውሉ ድርጅቶችና ቡድኖች ከ$40,000 እስከ $75,000 ለሚደርስ ድጋፍ ማመልከት ይችላሉ፣

- **በመስራት ላይራ ያሉ ፕሮግራሞችን ወይንም አገልግሎቶችን ማስፋፊያ:** በመስራት ላይ ያሉ ፕሮግራሞችን ወይንም አገልግሎቶችን ለማሳደግ ወይንም ለማስቀጠል የሚያስቡ ድርጅቶችና ቡድኖች ከ$40,000 እስክ $100,000 ለሚደርስ ድጋፍ ማመልከት ይችላሉ። እነኚህ ድርጅቶች በስራ ላይ ያለውን ፕሮግራም ወይንም አገልግሎት በማመልከቻቸው ላይ በግልጽ ማስረዳት ይጠበቅባቸዋል።

**ምሳሌዎች**

- አንድ የበጎ አድራጎት ድርጅት አዲስ የምግብ ዝግጅት ክበብ ለመጀመር አዲስ ማቀዝቀዣ መግዛት ይፈልጋል፣
- አንድ በርካታ ፕሮግራሞችና አገልግሎቶች ያሉት ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት ከፍተኛ ጥራት ያለው የህዝብ ግንኙነት ቪዲዮ ማዘጋጀት ይፈልጋል፣
- አንድ የምግብ እርዳታ የሚሰጥ ድርጅት የተገልጋይ አዛውንቶችን ፍላጎት ማሟላት እንዲችል ተቋሙን የማስተካከልና (መልሶ ማቋቋም) መኪና የመግዛት ፍላጎት አለው፣
- አንድ የመጠለያ አገልግሎት የሚሰጥ ተቋም በጊዜያዊ መጠለያነት ለሚቆዩ ወጣቶች የክረምት ኮቶች ይገዛል፣
- አንድ ቢ3 የሆነ ድርጅት ማህበረሰቡ ውስጥ አዲስ የወጣቶች መዝናኛ ፕሮግራም መጀመር ስልመቻሉ ጥናት ይጀምራል፣
- አንድ ቢ3 ለህብረተሰብ አገልግሎት የሚሰጥ ድርጅት ስደተኛ ለሆኑ ጥቁር ሠራተኞች ወሳኝነት ያለው ጥናትና ምርምር ለማድረግ አቅዷል፣
- አንድ ማህበረሰቡን መሰረት ያደረገ ድርጅት አንድ በሥራ ላይ ያለ ፕሮጄክቱ ላይ ጠንካራ የግምገማ ጥናት ያካሂዳል፤
- አንድ የጥቁር ወላጆች ስብስብ (ቡድን) የህብረተሰቡ አባላት የሆኑ ጥቁር አዛውንቶች የምግብ እጥረት እንዳይገጥማቸው የሚያግዝ ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት ማቋቋም ስለመቻሉ ማጥናት ይፈልጋል፣

Funded in part by the Government of Canada's Black-Led Philanthropic Endowment Fund | Canada

## የማህበረሰብ መዋዕለንዋይ (ካፒታል) ድጋፍ ዘርፍ | እስከ $250,000



ማህበራዊ መሰረታዊ ልማትና መዋዕለንዋይ ላይ ገንዘብ ማዋል

መመዘኛውን ያሟሉ ለጥቁር ማህበረሰቦች ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ መሰረተ ልማቶችን ወደፊት ለማራመድ ደፋርና ትልቅ ሀሳቦች ያላቸው ድርጅቶች። ድርጅቶች ፕሮግራሞችንና አገልግሎቶችን ለማሳደግና ወደ ንግድ ደረጃ ለማሸጋገር እስከ $250,000 ድረስ ድጋፍ መጠየቅ ይችላሉ። ይህ ድጋፍ አላማው ለማህበረሰባቸውና ለተሰማሩበት ዘርፍ ወሳኝ ሚና ያላቸው ድርጅቶችን በማገዝ ለጥቁሩ ማህበረሰብ ጠንካራ ስነምህዳር አስተዋጾ ማድረግና ስር-ነቀል ለውጥ ለማምጣት መሰረት ለመጣል ነው።

ይህ ድጋፍ በሀገር አቀፍ ደረጃ ቢያንስ ሁለት ክፍለሀገራትን በማካተት በተለያዩ አካባቢዎች ተሳትፎ ድርጅታዊና ህብረተሰባዊ መሰረተ ልማቶች ላይ በመሥራት የጥቁሩን ማህበረሰብ ፍላጎት የሚያግዝ ነው። ድርጅቶቹ የአዋጭነትና ፍላጎቶች ግምገማ የመሳሰሉ ጥናቶችን በማድረግ ድጋፍ የፕሮጄክቱ እንቅስቃሴና አሰራሩ የተሳካ እንድሚሆኑ፣ ማሳደግ እንድሚቻልና በሌሎች አካባቢዎችም ሊከናወኑ እንድሚችሉ ማሳየት ይጠበቅባቸዋል። አካላት

**የድጋፍ ማመልከቻ የሚያስገቡ በሙሉ የሁለት አመታት የሂሳብ መግለጫዎች፣ የድርጅታቸውን አመታዊ የስራ ማንቀሳቀሻ በጀትና፣ እስከአሁን ያከናወኑትን ሥራ የሚያሳይ ሪፖርት ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል።**

**ምሳሌዎች**

- አንድ ቢ3 ድርጅት ጥቁሮች የሚገለገሉበት የረጅም ጊዜ እንክብካቤ መስጫ (መጦሪያ) ቤት ማቋቋሚያ እቅዱ ማሳኪያ ድጋፍ ይጠይቃል፣
- አንድ በህረተሰብ ላይ የተመሰረተ (ኮሚኒቲ ቤዝድ) ድርጅት ከገቢ ጋር የተመጣጠነ መኖሪያ ቤት ግንባታ እቅድን ለማሳካት ድጋፍ ይጠይቃል፣
- አንድ ሴቶች ተኮር የሆኑ ድርጅቶች ስብስብ (ቡድን)በሚገኘው ድጋፍ ማዕከሉን በማስተካከል ከህገወጥ የሰዎች ዝውውር ሰለባነት ለተረፉ (ሰርቫይቨርስ) ሁለገብ የሆነ የተለያየ ድጋፍ ለመስጠት ይጠቀማል፣
- አንድ ቢ3 ድርጅት ከሌላ ሀገራት የሚመጡ (ማይግራንቶችና) ስደተኞችን ለማደራጀትና ለፍትህ ማጠናከሪያ እንቅስቃሴ የመሰረተ ልማት ድጋፍ ያደርጋል፣
- የጥቁር ገበሬዎችና አምራቾች ቡድን በአካባቢው የምግብ ፍትህ ለማስፈንና እጥረትን ለማስወገድ የሚያግዙ ተግባራትን ለመደገፍ እንዲሁም የንግድ ማእድ ቤቶች እንዲኖሩ ለማገዝ በጋራ የሚጠቀሙባቸው ማሽኖችንና መሳሪያዎችን መግዛት ያስባል።
- አንድ በገጠሩ ወይንም ሰሜናዊ ክፍል የሚገኝ ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት ጥቁር ሥራ ፈጣሪዎች፣ አነስተኛ የሥራ ተቋማትና፣ በግል ሥራ ተዳዳሪዎች የሚሰሩበት የጋራ የመሥሪያ ቦታ ይከፍታል፣

Funded in part by the Government of Canada's Black-Led Philanthropic Endowment Fund | Canada

# አመልካቾችን የመምረጥ ሂደት

መመዘኛውን ያሟሉ ድርጅቶች ያስገቡዋቸው ማመልከቻዎች በሙሉ የጥቁር ማህበረሰብ አባላት በሆኑ ሰዎች ተገምግመው ምርጫው ይከናወናል። መመዘኛውን የሚያሟሉት ድርጅቶች ካናዳ ውስጥ ያሉና የሚሰሩ ጥቁር መር፣ ጥቁር ተኮር፣ ጥቁር አገልጋይ የሆኑ የበጎ አድራጎትና ለትርፍ ያልተቋቋሙ ድርጅቶችና ቡድኖች ናቸው። አመልካቾች በሙሉ የማመልከቻቸውን ውጤት በማርች 2024 እንዲያውቁ ይደረጋል።

**የማህበረሰባዊ (ከማህበረስቡ የተውጣጡ)መራጭ ቡድኖች**

የማህበረሰብ የፕሮጄክት ምርጫ ቡድኖች ሁሉንም ማመልከቻዎች ከገመገሙ በኋላ ድጋፍ አሰጣጡን በተመለከተ ያላቸውን ምክረ ሀሳብ ለ ኤፍ.ኤፍ.ቢ.ሲ. ቦርድ ዳይሬክተሮች ያቀርባሉ። እነኚህ የማህበረሰብ የፕሮጄክት ምርጫ ቡድኖች የሚዋቀሩት 50% ከአመልካቾች የተውጣጡ ሲሆኑ ቀሪው 50% ደግሞ ከአጠቃላይ ማህበረሰቡ ይሆናል። ከአመልካቾች መሀከል የዚህ ቡድን አባል መሆን የሚሹ ማመልከቻቸውን በሚያስገቡበት ወቅት ይህንኑ ፍላጎታቸውን ማሳወቅ ይችላሉ። ይህ አሳታፊ የሆነ አሰራር አላማው ማህበረሰቦችን ማቀራረብ፣ ድጋፍ የሚያደርጉ አካላት አመራሮች ከተመረጡት ማህበረሰባት ጋር በቅርበት መስራት እንዲችሉ ማመቻቸት፣ መተማመንን መገንባት ማጎልበትና ማህበርሰብን መሰረት ያደረገ ጥቁር ተኮር ለውጥ የማምጣት ሂደትን መደገፍ ነው።



**የምርጫ መመዘኛዎች**

ሊየፕሮጀክት ድጋፍ ውሳኔዎች የሚወሰዱት መመዘኛውን ያሟሉ ቢ3 ድርጅቶች ለድጋፍ ያቀረቧቸው ፕሮጀክቶች  መመዘኛዎቹን ያሟሉበትን ደረጃ በመገምገም ይሆናል።

- ፕሮጄክቶቹ ድጋፍ የወጡትን የምርጫ መመዘኛዎች ማሟላት
  - ቢያንስ ከሶስቱ አንዱ የትኩረት አቅጣጫዎች ላይ መሥራት፣
  - አንድ ወይንም ከዛ በላይ የዘላቂ እድገት ግቦችና (ሰስቴይኔብል ጎልስ) የጤና ደረጃን የሚወስኑ ማህበርዊ ጉዳዮች (ሶሻል ዲተርምናንትስ ኦፍ ኸልዝ) ላይ መስራት፣
  - ድጋፍ የተጠየቀበት እንቅስቃሴ ባለው የስራ ማጠናቀቂያ በጀትና የጊዜ እደብ ውስጥ ለመከናወኑ እርግጠኛ መሆን፣
  - መመዘኛውን የማያሟሉ ተግባራትን አለማካተት፣
- ካናዳ ላሉ ጥቁር ማህበረሰቦች መልካም ውጤት ማስገኘት

Funded in part by the
Government of Canada's Black-Led
Philanthropic Endowment Fund
Canada

# ሪፖርት የማቅረብ ግዴታዎች

የድጋፍ ማመልከቻቸው ተቀባይነት ያገኘላቸው ድርጅቶች፡ ክፍያውን ከማግኘታቸው በፊት የድጋፍ ስምምነት የመፈረም አለባቸው። በድጋፍ ስምምነቱ መሰረት፡ ድጋፍ ተቀባዮቹ ሁለት ሪፖርት ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል። አላማችን ድጋፍ ከሚያገኙት ድርጅቶችና ቡድኖች ቀጣይነት ያለው ግንዛቤ ማግኘት፣ ትብብርን መገንባትና ማጠናከር፣ ማህበረሰቦችን መደገፍና ድጋፍ አሰጣጣችንን በመፈተሽ መማርም ጭምር ስለሆነ ሪፖርቶቹ አስፈላጊዎች ናቸው።

1 **ጠቅለል ያለ የመሀከለኛ ጊዜ ሪፖርት፡** ድጋፍ ከተሰጠበት ፕሮጀክት የጊዜ ገደብ አጋማሽ ላይ የኤፍ.ኤፍ.ቢ.ሲ. ባልደረባ የፕሮጄክቱን የእንቅስቃሴ እድገት ደረጃና ያጋጠሙትን ችግሮችና ውጤታማነቱን የሚገልጽ መረጃ ለመሰብሰብ ከድጋፍ ተቀባዩ ጋር ለውይይት ስብሰባ ይጠራል። ይህም መረጃ ልውውጥ በቪዲዮ ወይንም በስልክ ኮንፍረንስ ይከናወናል።

2 **የመጨረሻ ሪፖርት ማርች 31 2025** ላይ ወይንም ይህ ቀን ሳያልፍ ፕሮጄክቱ ድጋፍ ያገኘበትን እንቅስቃሴ ሲያጠናቅቅ ስለተከናወነው ሥራና ስለውጤቱ ሪፖርት ድጋፍ ተቀባዮቹ ሪፖርት ማቅረብ የጠበቅባቸዋል።

**በዚህ መልክ የሚሰበሰበው መረጃ ለካናዳ መንግስት ሊሰጥና ኤፍ.ኤፍ.ቢ.ሲ.ም ለሥራው ሊጠቀምበት ይችላል። ሆኖም ግን ኤፍ.ኤፍ.ቢ.ሲ. የሰዎችን የግል መረጃ ለካናዳ መንግስት እንደማያስተላለፍ እንዲያውቁለት ይፈልጋል።**

Funded in part by the Government of Canada's Black-Led Philanthropic Endowment Fund
Canada

# እንዴት ማመልከት እንደሚቻል

ርእባክዎን ማመልከቻዎትን ለማስገባት ዝግጁ ሲሆኑ ኢንተርኔት ላይ ያለውን የማመልከቻ መቀበያ ገጻችንን (ፖርታል) በመጠቀም ማመልከቻውን ያስገቡ። ማመልከቻው በሌላ ይዘት/ፎርም ድህረገጹ ላይ የሚገኝ ሲሆን ማመልከቻዎትን ከማስገባትዎ በፊት ሁሉንም መልስዎችዎትን እንዲጽፉና አስፈላጊ ሰነዶችን በሙሉ እንዲያያይዙ እንመክራለን። ማመልከቻዎትን አጠናቀው ከማስገባትዎ በፊት እንደ ረቂቅ (ድራፍት) ፋይል አድርገው ማቆየትና ተመልሰው ማንበብና ማሰተካከል ይችላሉ።

ማመልከቻዎትን በሚያዘጋጁበት ወቅት ድህረገጹ ላይ ያለውን የድጋፍ ስምምነት እንዲያነቡና እንዳነበቡትም እውቅና እንዲሰጡ ይጠየቃሉ። ይህንን ስምምነት በማመልከቻዎት ውስጥ ተካቶ ስላነበቡት ድጋፉ የሚያዘውን መከበር ያለበት የአተገባበር መመሪያ በግልጽ እንደተረዱ ከማሳየቱም ባሻገር እኛም ማመልከቻቸው ተቀባይ ለሆነ አመልካቾች ገንዘቡን በፍጥነትና በወቅቱ ማስተላለፍ ያስችለናል።

ማመልከቻውን በእንግሊዝኛም በፈረንሳይኛም ማግኘት ይችላሉ።

ማመልከቻቸውን በቃል ማስገባት ለሚፈልጉ አካላት ውሱን የሆኑ ዕድሎችን እንሰጣለን። ምርጫዎ ይህን መንገድ መጠቀም ከሆነ ይህንን ማስፈንጠሪያ በመጠቀም ማመልከቻዎትን በቃል ለማስገባት ቀጠሮ ማስያዝ ይኖርብዎታል። ይህን ሳያደርጉ ከቀሩ ማመልከቻዎ የመታየት እድል አይኖረውም። ማመልከቻውን በቃል ለማቅረብ ውሱን የሆነ ጊዜ ከጃንዋሪ 8 እስከ ጃንዋሪ 19/2024 ይኖራል።

ምናልባት፡ በሌላ ምክንያት ፖርታሉን ተጠቅመው ማመልከቻውን ማስገባት ካልቻሉ፡ እባክዎን የመጨረሻው የማመልከቻ መቀበያው ቀን ከመድረሱ በፊት በfund@forblackcommunities.org በመጠቀም የኤፍ.ኤፍ.ቢ.ሲ.ን ባልደረቦች በኢሜል ያግኙ። በተቻለን አቅም ሁሉ እናግዝዎታለን።

**ማመልከቻ ማስገቢያዎቹ ከዲሴምበር 18 ቀን 2023 ጀምሮ ለአመልካቾች ክፍት የሚደረጉ ሲሆን ማመልከቻዎቹ ተጠናቀው ከፌብሪዋሪ 1 ቀን 2024 ከምሽቱ 11:59 pm (በፓሲፊክ የሰዓት አቆጣጠር) አስቀድመው ለኤፍ.ኤፍ.ቢ.ሲ. መግባት አለባቸው።**

**የፖርታል ቁልፍ**

Funded in part by the Government of Canada's Black-Led Philanthropic Endowment Fund

Canada

# መርሀግብር

**ማመልከቻው መቀበል የሚጀመርበት ቀን**
18 de diciembre de 2023

**ማመልከቻ መቀበል የሚያበቃበት ቀን**
ፈብሪዋሪ 1 2024 በፓሲፊክ አቆጣጠር
ከምሽቱ 11 ሰአት ከ59 ደቂቃ

**ማመልከቻዎች የሚገመገሙበት ወቅት**
ፌብሪዋሪ 2024

**ለአመልካቾች ውሳኔው የሚነገርበት ወቅት**
ማርች 2024

**የገንዘብ ድጋፉ የሚሰጥበት ቀን**
ማርች 31 2024



Funded in part by the
Government of Canada's Black-Led
Philanthropic Endowment Fund

## የመገኛ አድራሻ

ምንም አይነት ተጨማሪ ጥያቄ ካለዎት fund@forblackcommunities.org በመጠቀም ያግኙን ወይንም ይህንን ማስፈንጠሪያ በመጠቀም የስብሰባ ቀጠሮ ይያዙ::

በስልክ ሊያገኙን ከፈለጉ **183 344 BLACK (442-5225)**

## ምስጋና

የብሪጅ ኤንድ ቢልድ ድጋፍ (ፈንድ) በካናዳ መንግስትና::

Funded in part by the Government of Canada's Black-Led Philanthropic Endowment Fund | Canada